የሰ/መ/ቁ. 20212

ግንቦት 29 ቀን 1998

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ወ/ሮ አብረኸት ተክሉ

ተጠሪ፡- አቶ ገዛኢ ገ/ፃዲቅ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ፣

ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትና ቦታ አመልካች ከባለቤቷ ጋር ያፈሩትው የጋራ ሀብት ነው በማለት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሣኔ በመሻሩ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ከተወሰነ በኋላ የግራ ቀኙ ክርክር ተሰምቷል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ለመሻር መሠረት ያደረገው የአሁኑ ተጠሪ ክርክር የተነሣበትን ቤትና ቦታ አስመልክቶ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የተረጋገጠ የሽያጭ ምዝገባ አቅርቧል በሚል እንደሆነ ከውሣኔው መረዳት ችለናል፡፡ በዚህ መዝገብ ከአጠቃላዩ ሁኔታ መረዳት የቻልነው ዋነኛ ነገር አሁን አከራካሪ በሆነው ቦታ ላይ የአሁኗ አመልካች ቀደም ሲል ከባለቤቷ ጋር 125 ካ.ሜ ቦታ ገዝተውና ቤት ሠርተው ሲኖር መቆየታቸውን፣ በመካከላቸው በተፈጠረው አለመግባባት እንዲለያዩ ሲወሰን ንብረትን አስመልክቶ አሁን ክርክር ካስከተለው ቦታ ላይ የሚገኘውን ቤትና ቦታ በጋራ እንዲካፈሉ በ06/11/94 ውሣኔ በማኅበራዊ ፍ/ቤት ተሰጥቶ ይህም በይግባኝ ፀድቆ ያደረገ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ የክርክሩ ተካፋይ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን 1/10/98

ሆኖ ፍርዱን ያስለወጠበት ሁኔታ አለመኖሩንም ይህ ችሎት በሚገባ ተረድቷል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ከዚህ ሁሉ ሕጋዊ ክንዋኔ በኋላ ቀደም ሲል በ1984 በቃል ስምምነት ብቻ ከወ/ሮ ፈቱን 125 ካ.ሜ. ቤትና ቦታ ገዝቼ ማዘጋጃ ቤቱ ስሙን አላዞርም ስላለኝ በድጋሚ ስምምነት በ1995 ተደርጎ ጠቅላላ ስፋቱ 240 ሜ.ካ የሆነ ቦታና ቤት ገዝቻለው ብሎ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ውሉን አስመዝግቦ ተገኝቷል መባሉ ብቻ ቀደም ሲል 125 ካ.ሜ. ቦታና ቤት ላይ በሕግ አግባብ ሥልጣን በተሰጠው ማኅበራዊ ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ፍርድ የሚያሽር ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን መሠረታዊ የሕግ ነጥብ በማለፍ የአሁኑ ተጠሪ 240 ካ.ሜትር ቤትና ቦታ ብቸኛ ባለቤት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ26/8/97 በመዝገብ ቁጥር 02108 የሰጠው ውሣኔ በከፊል ተሻሽሏል፡፡
- የአሁኗ ተጠሪ አከራካሪ ከሆነው 240 ካ.ሜትር ቦታ ውስጥ 125 ካ.ሜትር ቦታ ላይ ያረፈው ቤትና ቦታ ከባለቤቷ ጋር በጋራ ያፈሩችው ንብረት ነው ብለናል፡፡
- ይህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ በቀረው ቦታ ላይ ያለውን መብት የሚነካ አይሆንም፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ____ ቀን 1/10/98

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ